# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የሥራና ክህሎት ቢሮ

# የመንግስት የማስልጠኛ ተቋማትና ከግል ድርጅቶች ጋር በአጋርነት (PUBLIC PRIVATE PARTNERSHIP) የሚሰሩበት መመሪያ

መስከረም 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ


ክፍል አንድ ........ 4
1. ጠቅላላ ድንጋጌዎች ........ 4
1.3 ዎታ አገላለፅ ........ 5
1.4 ተፈፃሚነ ትወሰን ........ 6
1.5. ዓላማ ........ 6
1.6. አስፈላጊነት ........ 6
1.7. የአጋርነት ፅንሰ ሀሳብ፣ መርሆዎችና የተፈፃሚነት ወሰን ........ 7
1. የአጋነት ፅነሰ ሀሳብ ........ 7
1.8. የአጋርነት መርሆዎች ........ 7
1.9. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 7
ክፍል ሁለት ........ 8
2. የአጋርነት የአሰራር ስርዓት ........ 8
2.1 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስራና ክህሎት ቢሮ ተግባርና ሀላፊነት ........ 8
2.2 የማሰልጠኛ ተቋማት ተግባርና ሀላፊነት ........ 8
2.3 አጋርነት የሚፈጠርበት ሁኔታ ........ 9
2.4 ውል የማዘጋጀት ስልጣን ........ 10
2.5 ውል ስለማጽደቅ ወይም ስለማሻሻል ........ 10
2.6 የውል ተፈራራሚ አካላት መብትና ግዴታ ........ 10
5. የአጋርነት ስራዎች ቁጥጥርና ግምገማ ........ 12
6. የአጋርነት የውል ስምምነት የቆይታ ጊዜ ........ 12
7. የግጭት አፈታት ........ 13
8. የተጠያቂነት ስርዓት ........ 13
9. ውል ስለማቋረጥ ........ 13
ክፍል ሶስት ........ 14
3. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 14
3.1. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች ........ 14
4.2. መመሪያን ስለማሻሻል ........ 14
4.3. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ ........ 14

## መመሪያ ቁጥር----/2018 ዓ.ም

## የመንግስት የማሰልጠኛ ተቋማትና ከግል ድርጅቶች ጋር በአጋርነት (PUBLIC PRIVATE PARTNERSHIP) የሚሰሩበት መመሪያ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የመንግስት ተቋማት መንግስት በሚመድብላቸው በጀት ብቻ የተሰጣቸዉን ተልእኮ ለማሳካት በቂ አለመሆኑ ታምኖበት የራሳቸውን የዉስጥ ገቢ ምንጭ እንዲፈጥሩና እንዲያስፋፉ የመንግስት እና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010 መሰረት የመንግስት የማሰልጠኛ ተቋማትና ከግል ድርጅቶች ጋር በአጋርነት (PUBLIC PRIVATE PARTNERSHIP) የሚሰሩበት መመሪያ ወጥቶለት መሰራት እንዳለበት አስፈላጊቱ ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 የወል የአስፈፃሚ አካላት ላይ አንቀጽ 16(2) (ሠ) መሰረት ይህ መመሪያ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን PPP ስራዎች ዝርዝር አፈጻጸም ለመወሰን ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# 1. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1.1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የመንግስት የማሰልጠኛ ተቋማትና ከግል ድርጅቶች ጋር በአጋርነት (PUBLIC PRIVATE PARTNERSHIP) የሚሰሩበት መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1.2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማለት ነው፤
2. "ቢሮ" ማለት የሥራና ክህሎት ቢሮ ነው፤
3. **"ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ"** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ ከደረጃ 1 (አንድ) እስከ ደረጃ 5 (አምስት) ድረስ ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጥ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ማለት ነው፤
4. **"ኮሌጅ"** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮከ ደረጃ

   1(አንድ) እስከ ደረጃ 4(አራት) ድረስ ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጥ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ማለት ነው፤
5. **"ቅርንጫፍ ተቋም (ካምፓስ)"** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ወይም ኮሌጅ ስር እንዲተዳደሩ የተቋቋሙ ተቋማት ማለት ነው፤
6. **"የማሰልጠኛ ተቋማት'** ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ ሥር የሚተዳደሩ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችን፣ ኮሌጆችንና የምርታማነት ማሻሻያና

የልህቀት ማዕከል ማለት ነው፤

7. ‘የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት እና የግል ድርጅቶች አጋርነት” ማለት ሁለቱ ተቋማት የጋራ ራዕይ፣ ግብና ዓለማ ይዘው በጋራ በመስራት ተጠቃሚ ለመሆን የሚፈጥሩት አጋርነት ነው፤
8. "የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና" ማለት በሃገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት በማንኛውም የሙያ ዘርፍ ደረጃቸው ከከፍተኛ ትምህርት በታች በሆኑ መደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ መልኩ የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ነው፤
9. "መደበኛ ስልጠና" ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት 12ኛ ክፍል ላጠናቀቁ ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ስምንት ድረስ የሚሰጥ ስልጠና ነው፤
10. "የአጫጭር ጊዜ ስልጠና" ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከሙያ ደረጃው ውስጥ ወደ ስራ ሊያሰማሩ የሚችሉ የብቃት አሀዶችን በመለየት የስልጠና ሞጁሎችን አዘጋጅቶ ሰልጣኞችን ከስራ ጋር ለማስተሳሰር የሚሰጥ ስልጠና ነው፤
11. "የኢንኩቤሽን አገልግሎት" ማለት የሥራ ፈጠራና አዳዲስ የቴክኖሎጂ ሃሳብ ያላቸውን ግለሰቦች ወይም ተቋማት ሀሳባቸውን ወይም በእጃቸው ያለ የተረጋገጠ ምርትን ወይም ቴክኖሎጂን እንዲያለሙ የሚሰጥ የሙያ እና የመሳሪያ ወይም የማቴሪያል ድጋፍ ነው፤
12. "ሰልጣኝ" ማለት ሙያ ለመቅሰም እና ያለውን ችሎታ የሙያ ስነምግባር እና አመለካከት ለማዳብር ሲባል በተቋም በኢንዱስትሪ እና በትብብር በሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መርሀ ግብር ውስጥ ስልጠና የሚከታታል ነው፤
13. "አሰልጣኝ" ማለት በሙያው የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ብቁ የሆነና የማሰልጠን ስነ ዘዴ ስልጠና ወስዶ በማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ የሚያሰለጥን ነው፤
14. "የትብብር ስልጠና" ማለት ሰልጣኞች በማሰልጠኛ ተቋማት የመነሻ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና ከሰለጠኑ በኋላ በማሰልጠኛ ተቋማት ከአምራች ኢንዱስትሪዎች እና ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር በሚደረግ የውል ስምምነት መሰረት በሙያቸው በኢንዱስትሪው ውስጥ እንዲሰለጥኑ ማድረግ

ነው፤

15."**የኢንዱስትሪ ውስጥ ስልጠና**" ማለት በኢንዱስትሪው እና በማሰልጠኛ ተቋማት ትብብር የሚሰጥ የኢንዱስትሪ ሙያተኞችን እና በመንግስት ማሰልጠኛ ተቋማት የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞችን ሙያዊ ብቃትን ለማሳደግ የሚሰጥ እውቀትን ከክህሎት ጋር ለማዋሀድ የሚያስችል ስልጠና ነው፤

16.“**የግል አምራች ድርጅት**” ማለት ጥሬ እቃዎችን በመጠቀም ምርት የሚያመርት ህጋዊ ፈቃድ ያለው ድርጅት ነው፤

17.“**የግል አገልግሎት ሰጪ ድርጅት**” ማለት ለደንበኞች አገልግሎት የሚሰጥ ህጋዊ ፈቃድ ያለው ድርጅት ነው፤

18. "**ፕሮሰስ ካውንስል**" የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ወይም ኮሌጅ ውስጥ የትምህርትና ስልጠና እና የማኔጅመንት አባላትን ያካተተ ካውንስል ማለት ነው፤

19. "**ቦርድ**" ማለትበአዋጅ በተቋቋሙና በክላስተር በተደራጁ የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆችማለት ነው።

## 1.3 ፆታ አገላለፅ

ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።

## 1.4 ተፈፃሚነ ትወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራና ክህሎት ቢሮ ስር በሚገኙ የመንግስት ኮሌጆች እና የምርታማነት ማሻሻያና የልህቀት ማዕከል እና አጋር ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## 1.5. ዓላማ

በመንግስት የቴክኒክና ሙያ የማሰልጠኛ ተቋማትና በግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መካከል በግልፀኝነት እና በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የአጋርነት አሰራር ስርዓት በመዘርጋት የስልጠና ጥራትና አግባብነትን በማረጋገጥ የምርት ጥራት፣ ምርታማነትንና የአገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል የከተማዋን ነዋሪ ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ ነው።

## 1.6. አስፈላጊነት

ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት በተፈጠረው የገበያ ስርዓት በምርት ጥራት አቅርቦትና በዋጋ ተወዳዳሪ መሆን የግድ ይላል፡፡ በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ተቋማትና የግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በአጋርነት መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት፡-

1. በማሰልጠኛ ተቋማትና በግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር የተጠናከረ አጋርነት በመፍጠር የሚሰጡ ስልጠናዎች ጥራትና አግባብነትን ለማረጋገጥ፤
2. በአምራች እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሰራተኞች ሙያዊ ብቃታቸውን በማሳደግ በምርት ጥራት፣ አቅርቦት፣ በዋጋ እና በአገልግሎት አሰጣጥ ተወዳዳሪ ለማድረግ፤
3. የሚፈጠረው አጋርነት በጋራ ራዕይ፣ ግቦችና ዓለማዎች ላይ የተመሰረተ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ያለው የአጋርነት የአሰራር ስርዓትን ለመዘርጋት፤
4. በአምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በአጋርነት በመስራት ልምድ ለመለዋወጥና አዳዲስ ፈጠራዎችን በጋራ ለመስራትና ለመጠቀም፤
5. በሁለቱም አካላት ያለውን ሰብአዊና ቁሳዊ (አሰልጣኝ፣ የማሰልጠኛ ማሽነሪዎች፣ የመሰሪያ ቦታ) የግብአት ብክነቶችን በመከላከል በጋራ ለመጠቀም፤
6. የትምህርና ስልጠና ፖሊሲ ከማስፈጸም አኳያ የስልጠና ማቴሪያል ዝግጅትና ክለሳ የኢንዱስትሪውን ሙያተኞች በአጋርነት በማሳተፍ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት፡፡

## 1.7. የአጋርነት ፅንሰ ሀሳብ፣ መርሆዎችና የተፈፃሚነት ወሰን

### 1. የአጋርነት ፅነሰ ሀሳብ

የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋማትና የግል ድርጅቶች አጋርነት ጽንሰ-ሀሳብ የሁለቱም ሴክተሮች ማለትም የመንግስት እና የግል ኢንዱስተሪዎች ጠንካራ ጎኖችን በመጠቀም አንዳቸውም በግል ሊያሳኩት የማይችሉትን ውጤት ለማስመዝገብ የጋራ ቁርጠኝነትን ያካትታል፡፡ እነዚህ አጋሮች በጋራ ጥቅም፣ ስጋትን መጋራት እና የጋራ ግቦችን ዋና መርህ በማድረግ መስራት ይገባቸዋል፡፡

### 2. የአጋርነት መርሆዎች

1. የማሰልጠኛ ተቋማቱና አጋር ድርጅቶች የጋራ ራዕይ (Shared Vision)፣ ግቦችና

ዓላማዎቻቸውን ለማሳካት በጋራ መስራት፤

2. የማሰልጠኛ ተቋማቱና አጋር ድርጅቶች በጋራ በማቀድና ውሳኔዎችን በማሳለፍ ውጤታማ አፈጻጸም እንዲኖር ማስቻል፤
3. የማሰልጠኛ ተቋማቱና አጋር ድርጅቶች ቁሳዊና ሰባዊ ግብአቶችን በጋራ በመጠቀም የግብአት ብክነትን በማስወገድ ሁለቱንም አካላት ተጠቃሚ ማድረግ፡፡
4. የማሰልጠኛ ተቋማቱና አጋር ድርጅቶች አጋርነት ቀጣይነት ያለው መሻሻል እንዲኖር ተለማጭ ሆኖ እየተከለሰ ቀጣይነት ያለው መሻሻል በየጊዜው የሚያስመዘግብ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 1.9. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ባሉ የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትና ጋር አጋርነት በፈጠሩ የግል አምራች/ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መካከል ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2. የአጋርነት የአሰራር ስርዓት

### 2.1 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስራና ክህሎት ቢሮ ተግባርና ሀላፊነት

1. ከማሰልጠኛ ተቋማት ጋር አጋርነት ለሚፈጥሩ የግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተገቢውን ግንዛቤ መፍጠር፤
2. የማሰልጠኛ ተቋማት ስልጠና በሚሰጡባቸው ሙያዎች ላይ ተመስርተው ከግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር አጋርነት እንዲፈጠር አቅጣጫ ይሰጣል ያስተባብራል፤
3. የአጋርነት የውል ስምምነቱ በጋራ ራዕይ፣ ግቦችና ዓላማዎች ላይ የተመሰረተ መሆኑን ይከታተላል፤
4. በአጋርነት የውል ፎርማው ላይ ግብዓትን (የስበዓዊ፣ ማሽነሪና የመስሪያ ቦታ) በጋራ የመጠቀም ሂደት በውስጥ ገቢ ደንብ መሰረት ተፈፃሚ መሆኑን ይከታተላል፤
5. በአጋርነት በሚሰሩ ስራዎች የተሻለ አፈፃፀም ላላቸው የመንግስት የማሰልጠኛ ተቋማትና የግል አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የማበረታቻ እውቅና ይሰጣል።

### 2.2 የማሰልጠኛ ተቋማት ተግባርና ሀላፊነት

1. የልማት ፀጋን መሰረት አድርገው ከሚሰጡት ስልጠና ጋር ተስማሚ የሆኑ እና አጋርነት የሚፈጥሩባቸውን የግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን መለየት፤
2. አጋርነት የሚፈጥሩባቸው አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ግንዛቤ ማስጨበትና ፍላጎታቸውን ማወቅ፤
3. አጋርነት የሚፈጠርባቸው አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ራዕይ፣ግቦችና ዓላማዎች ከማሰልጠኛ ተቋሙ ጋር የሚጣጣሙና በጋራ ሊያሰሩ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
4. የጋራ ራዕይ፣ ግቦችና ዓላማዎችን በመንደፍ አጋርነት ከሚፈጠርባቸው ድርጅቶች ጋር መወያየትና ማዳበር፤
5. ውጤታማ ሊያደርጋቸው በሚችል ስልጠና በሚሰጡባቸው ሙያዎች በአጋርነት ሊሰሩ የሚችሉ አጋር ድርጅቶች ጋር ለመስራት የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ አጋርነት መፍጠር፤

6. የጋራ በተደረገው ራዕይ፣ ግቦችና ዓላማዎች መሰረት የጋራ ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት፤

7. በአጋርነት ሊሰሩ ከሚችሉ ድርጅቶች ጋር የሚሰሯቸውን ፕሮጀክቶች ለከተማ አስተዳደሩ የመንገስትና የግል አጋርነት ጽ/ቤት እና ለቢሮ በማሳወቅ ማስፈቀድ፤

8. በአጋርነት ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር የሚፈጸሙ ፕሮጀክቶች ህጋዊ በሆነ የውል ስምምነት እንዲፈጸም ማድረግ፤

9. በአጋርነት የሚፈጸሙ ፕሮጀክቶችን የስራ እቅድና አፈጻጸም በየወቅቱ በመገምገም ውጤቶችን ለቢሮ ሪፖርት ማድረግ፤

10. በአጋርነት የሚፈጸሙ ፕሮጀክቶች የገንዘብ አስተዳደር በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መሆኑን ማረጋገጥ፤

11. በአጋርነት የሚፈጸሙ ፕሮጀክቶች ሰነዶችን መያዝና ለኦዲት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ፤

12. በአጋርነት የሚፈጸሙ ፕሮጀክቶች በተከታታይ ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት እንዲፈጸሙ ማድረግ፤

13. በአጋርት የሚፈጸሙ ፕሮጀክቶች ለተቋሙ ያመጡትን ለውጥ በጥናት ማረጋገጥ፤

## 2.3 አጋርነት የሚፈጠርበት ሁኔታ

**የማሰልጠኛ ተቋማቱ አጋርነት የሚፈጥሩበት ሁኔታዎች፤**

1. የማሰልጠኛ ተቋማቱ በአጋርነት ሊሰራቸው የሚፈልጉባቸውን ተግባራት ግልጽ ጨረታ በማውጣት አጋር ድርጅቶችን ይጋብዛሉ፤
2. ከማሰልጠኛ ተቋማቱ ጋር በጋራ ለመስራት ፍላጎት ያላቸው ድርጅቶች በሚያቀርቡት ፍላጎት መሰረት አጋርነት ሊፈጠር ይችላል፤
3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተጠቀሰ አጋርነት እንደተጠበቀ ሆኖ የአጋርነት ውሉ የሚጸድቀው እስከ 10 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ድረስ በማሰልጠኛ ተቋማቱ ፕሮሰስ ካውንስል ይሆናል፤
4. የአጋርነት ውሉ ከ10 ሚሊየን በላይ እስከ 30 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ድረስ ከሆነ በክላስተሩ ቦርድ ያስወስናል፤
5. የአጋርነት ውሉ ከ30 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር በላይ ከሆነ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥትና የግል አጋርነት ፅ/ቤት ያስዎስናል፤

4. በከተማ አስተዳደሩ የግልና የመንግስት አጋርነት ጽ/ቤት በሚቀርብ ጥያቄ

የሚፈጸም የአጋርነት ውል በጽ/ቤቱ የአሰራር ስርዓት መሰረት ይሆናል፡፡

## 2.4 ውል የማዘጋጀት ስልጣን

የመንግስት ማሰልጠኛ ተቋማት በአጋርነት ለመስራት ከለዩዋቸው አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅች ጋር ያቀዷቸውን እቅዶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚፈራረሙበት የውል ስምምነት በዚህ መመሪያ በቀረበ የመዋዋያ ቅጽ መሰረት ይሆናል፡፡

## 2.5 ውል ስለማጽደቅ ወይም ስለማሻሻል

1. የተዘጋጀውውል የማሰልጠኛ ተቋማቱ የፕሮሰስ ካውንስል ገምግሞና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመግባባት እንዲጸድቅ ይደረጋል፤
2. በስራ ዘመኑ የገበያ ጥናት መሰረት በማድረግ ውሉን ሊያሻሽል ይችላል፤

## 2.6 የውል ተፈራራሚ አካላት መብትና ግዴታ

በአጋርነት ለመስራት የተፈራረሙ የመንግስት ተቋማትና የግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በተስማሙበት በጋራ የሚፈጸሙ ፕሮጀክቶች ላይ ግዴታቸውን በመወጣት መብታቸውን ለመጠቀም የተጠያቂነት ስርዓትን መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡

### 1. የቴክኒክና ሙያ ማስልጠኛ ተቋማት መብት

ሀ. በውል ስምምነቱ መሰረት ሰልጣኞችና አሰልጣኞች አጋርነት በተፈራረሙ የግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ እንዲሰለጥኑ የማድረግ፤

ለ. አጋርነት በፈጠረባቸው አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ባለው ክፍት ቦታ ብቁ የሆኑ ስልጠና አጠናቃቂዎችን የስራ ዕድል እንዲያገኙ የማድረግ፤

ሐ. አጋርነት የተፈጠረባቸው አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በስርዓተ ስልጠና እና በስልጠና ማቴሪያል ዝግጅት በጋራ እንዲሰሩ የማድረግ፤

መ. በውሉ መሰረት የታቀዱ ዕቅዶች በግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲከናወኑ የመጠየቅ፤

ሠ. በአጋርነት የስራ ክንውን የሚፈጠሩ አዳዲስ አሰራሮችንና ፈጠራዎችን በጋራ የመጠቀም፤

ረ. አጋርነት የተፈጠረባቸው አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በውሉ መሰረት ተግባራትን ማከናወን ካልቻሉ ውሉን የማቋረጥ፡፡

## 2. የግል አምራች/አገልሎት ሰጪ ድርጅቶች መብት

ሀ. አጋርነት በፈጠሩባቸው የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ባለሙያዎቻቸው ስልጠና አግኝተው ሙያዊ ብቃታቸው እንዲያድግ የማድረግ፤

ለ. ከስልጠና ስዓት ውጪ በውል የማሰልጠኛ ማሽነሪዎችን በውስጥ ገቢ ደንብ መሰረት የመጠቀም፤

ሐ. የምርት ጥራታቸውንና ምርታማነታቸውን/አገልግሎት አሰጣጣቸውን የሚያሳድግ ሙያዊ ድጋፍ የማግኘት፤

መ. ለቅጥር ብቁ ስልጠና አጠናቃቂ ባለሙያዎችን/ብቁ ሰልጣኞችን የማግኘት፤

ሠ. በስልጠና ጥራትና አግባብነት ላይ የሚታዩ ክፍተቶች እንዲሻሻሉ ጥያቄ የማቅረብ፤

ረ. ውሉ መሰረት የታቀዱ ዕቅዶች አጋርነት ከፈጠሩባቸው የማሰልጠኛ ተቋማት በአግባቡ እንዲከናወኑ የመጠየቅ፤

ሸ. በአጋርነት የስራ ክንውን የሚፈጠሩ አዳዲስ አሰራሮችንና ፈጠራዎችን በጋራ የመጠቀም፤

ቀ. አጋርነት የፈጠሩባቸው የማሰልጠኛ ተቋማት በውሉ መሰረት ተግባራትን ማከናወን ካልቻሉ ውሉን የማቋረጥ፣

## 3. የቴክኒክና ሙያ ማስልጠኛ ተቋማት ግዴታ

ሀ. የአምራች/አገልግሎት ሰጪ የግል ድርጅትን ሰራተኞች የክህሎት ክፍተት በመለየት ማብቃት፤

ለ. የአምራች/አገልግሎት ሰጪ የግል ድርጅትን ሰራተኞች የትምህርት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ የትምህርትና ስልጠና ዕድል መስጠት፤

ሐ. የአምራች/አገልግሎት ሰጪ የግል ድርጅቶች ለመቅጠር የሚፈልጓቸውን ባለሙያዎች በብቃትና በጥራት አሰልጥኖ ማቅረብ፤

መ. ለአምራች/አገልግሎት ሰጪ የግል ድርጅትን ግብአቶችን (መሽነሪ፣ የመስሪያ ቦታ) በውሥጥ ገቢ ደንብ መሰረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ፣

ሠ. አጋርነት ከተፈጠረባቸው አምራች/አገልግሎት ሰጪ የግል ድርጅቶች የምርት ጥራትና ምርታማነታቸውና የአገልግሎት አሰጣጣቸውን የሚያሻሽሉ ሙያዊ ድጋፎችን የመስጠት፣

ረ. አጋርነት ከፈጠሩባቸው አምራች/አገልግሎት ሰጪ የግል ድርጅቶች የስልጠና አሰጣጥ ሂደቱ ወይም ስርዓተ ስልጠናው እንዲሻሻል ጥያቄ

ሲያቀርቡ ተቀብሎ የማሻሻል፣

## 4. የግል አምራች/አገልሎት ሰጪ ድርጅቶች ግዴታ

ሀ. ከማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በተስማሙበት ውል መሰረት በድርጅቱ ውስጥ ሰልጣኞችንና አሰልጣኞችን በማሰልጠን ማብቃት፤

ለ. በስርዓተ ስልጠና ዝግጅት እና ስልጠና በመስጠት ሂደት በጋራ መስራት፤

ሐ. ከስልጠና ስዓት ውጪ በተቋማት ለሚጠቀሙበት ግብአት (ማሽነሪዎች፣ የመስሪያ ቦታ ወ.ዘ.ተ) በውስጥ ገቢ ደንብ መሰረት ተገቢውን ክፍያ የመፈፀም፣

መ. በጋራ የታቀደው ዕቅድ በአግባቡ የመፈፀም፣ በጋራ የመገምገም፣ እና የማሻሻል ስራዎች በአጋርነት መስራት፣

## 5. የአጋርነት ስራዎች ቁጥጥርና ግምገማ

1. የመንግስት ቴ/ሙ/ማሰልጠኛ ተቋማትና የግል አምራችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የአጋርነት የስራ ክንውን በቢሮ፣ በማሰልጠኛ ተቋማትና በግል ድርጅቶች ክትትልና ግምገማ ይደረግበታል፤
2. የአጋርነት ስራው አፈፃፀምን በየ ስድስት ወሩ በቦርድ እየተገመገመ ለሚታዩ ክፍተቶች በክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፤
3. በመንግስት ማሰልጠኛ ተቋማት ደረጃ በየወሩ በማኔጅመንቱ እየተገመገመ ለሚታዩ ክፍተቶች በወቅቱ መፍትሄ እንዲያገኙ ይደረጋል፤
4. እንዲሁም ማሰልጠኛ ተቋማት እና በአጋርነት የሚሰሩ የግል አምራችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ተወካዮች ባሉበት በየ6 ወሩ እየተገመገመ የማስተካከየ ስራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

## 6. የአጋርነት የውል ስምምነት የቆይታ ጊዜ

የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትና የግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የአጋርነት የቆይታ ጊዜ የወቅቱ የገበያ ሁኔታ እየታዩና ውጤታማነቱ በጊዜው እየተገመገመ እየታደሰ የሚቀጥል ወይም የሚቋረጥ ይሆናል፡፡

## 7. የግጭት አፈታት

የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትና በአጋርነት ከሚሰሩ አምራች/አገልግሎት ሰጪ የግል ድርጅቶች የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በውይይት የሚፈቱበት የአሰራር ስርዓት በኮሌጁ የሚዘረጋና ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ከኮሌጁ አቅም በላይ ከሆነ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ አማካኝነት በውይይት እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ ይህ ካልሆነ በውል ስምምነታቸው መሰረት በህግ አግባብ የሚፈታ ይሆናል፡፡

## 8. የተጠያቂነት ስርዓት

1.ከዚህ መመሪያ ውጭ የአጋርነት ውል የፈጸመና ተግባራዊ ያደረገ አካል ተጠያቂ ይሆናል፤

2.በፈጠሩት የአጋርነት የውል ስምምነት መሰረት በወቅቱ ተቋሙ ማግኘት ያለበትን ገቢ ያላስገባ አካል ተጠያቂ ይሆናል፤

3.ማንኛውም ወጭና ገቢ ህጋዊ የኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ስርዓትን ተከትሎ ተፈጻሚ ካልተደረገ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

## 9. ውል ስለማቋረጥ

በውል ስምምነቱ መሰረት ከሁለት አንዱ ወገን ግዴታውንና ሃላፊነቱን ካልተወጣና ከአጋርነት ስምምነቱ ውጪ ተግባር ፈፅሞ ከተገኘ የውል ስምምነቱ በየትኛውም ጊዜ በተናጠልም ሆነ በጋራ ሊቋረጥ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## 3. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 3.1. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረኑ መመሪያዎች፣ አሰራርና ልማዶች በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የፋይናን መመሪያዎች መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

### 3.2. መመሪያን ስለማሻሻል

ይህንን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ቢሮው ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### 3.3. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በስራና ክህሎት ቢሮ ጸድቆ ከወጣበት ቀን---2018 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

## የአጋርነት የውል ስምምነት

### አንቀፅ 1፡ መግቢያ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ አግባብነት፣ ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን የማሳደግ ዓላማን መሰረት በማድረግ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እና የግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በጋራ በመስራት ለሁለቱም ተቋማት እና ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡

በዚህ መሠረት፣ በጋራ ራዕይ፣ ግቦችና ዓላማዎች ላይ የተመሰረተ ውጤታማ የአጋርነት ግንኙነት በመፍጠር፣ ተፈፃሚነቱን በመገምገምና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ በጋራ ለመስራት ይህንን የአጋርነት ውል ስምምነት ፈጽመናል፡፡

### አንቀፅ 2፡ ተዋዋይ ወገኖች

**አንደኛ ተዋዋይ ወገን** (የኮሌጁ ስም):

1. ስም፡የ.................................................................................................................................... ኮሌጅ
2. አድራሻ፡ (ከተማ/ክፍለ ከተማ)፡................................... (ፖ.ሣ.ቁ)፡................................... (ስልክ ቁጥር)፡...................................
3. በህግ የሚወክለው (የኃላፊው ስም እና ማዕረግ): ..........................................................................................

**ሁለተኛ ተዋዋይ ወገን** (የድርጅቱ ስም):

1. ስም፡ .................................................................የግል አምራች/አገልግሎት ሰጪ ድርጅት
2. አድራሻ፡ (ከተማ/ክፍለ ከተማ)፡................................... (ፖ.ሣ.ቁ)፡................................... (ስልክ ቁጥር)፡...................................
3. የንግድ ፈቃድ ቁጥር፡ ..........................................................................................
4. በህግ የሚወክለው (የኃላፊው ስም እና ማዕረግ): ..........................................................................................

### አንቀፅ 3፡ የውሉ ዓላማዎች

የዚህ የአጋርነት ውል ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. **ብቁ ባለሙያዎችን ማፍራት፡** በስራ ገበያው ፍላጎት መሰረት ብቁ፣ ተወዳዳሪ እና የሥራ ክህሎታቸው ያደገ ብቁ ባለሙያዎችን በጋራ ለማፍራት፡፡
2. **ምርታማነትን ማሳደግ፡** የምርት ጥራትና ምርታማነትን/የአገልግሎት አሰጣጥን በኮሌጁ ስልጠናና ጥናት እንዲሁም በድርጅቱ ተሞክሮ በማሳደግ ውጤታማ ድርጅቶችን መፍጠር፡፡
3. **የተግባር ስልጠናን ለማስፋት፡** የኮሌጁ ሥርዓተ ትምህርት ከድርጅቱ የሥራ ሂደት ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ እና ለተማሪዎች የተሟላ የሥራ ላይ ልምምድ ዕድል መፍጠር፡፡

## አንቀፅ 4፡ <u>የአጋርነት ወሰንና የሁለቱ ወገኖች ኃላፊነት</u>

### ሀ. የኮሌጁ ኃላፊነቶች፡

1. **የሥልጠና ድጋፍ፡** በድርጅቱ ፍላጎት መሠረት ልዩ የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችንና የምክር አገልግሎት መስጠት።
2. **የተማሪ ምደባ፡** ስልጠናቸውን ያጠናቀቁ እና በድርጅቱ መስክ የተካኑ ተማሪዎችን ለሥራ ላይ ልምምድ መመደብ።
3. **የሙያ ድጋፍ፡** ለድርጅቱ ሠራተኞች የሙያ ብቃት ምዘናና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት።

### ለ. የአጋር ድርጅቱ ኃላፊነቶች፡

1. **የሥራ ላይ ልምምድ ዕድል፡** ከኮሌጁ ለተመደቡ ተማሪዎች ምቹ የስልጠና ቦታ፣ አስፈላጊ ቁሳቁስና መካሪ (Mentor) መመደብ።
2. **ግብረመልስ መስጠት፡** በሥርዓተ ትምህርት፣ በቴክኖሎጂ እና በሥልጠና አግባብነት ላይ ለኮሌጁ ተጨባጭና ወቅታዊ ግብረመልስ መስጠት።
3. **ግብአት ማቅረብ፡** ለኮሌጁ የተግባር ስልጠና የሚያግዙ ቁሳቁሶች፣ ማሽነሪዎች ወይም የፋይናንስ ድጋፍ (በስምምነት) ማድረግ።

## አንቀፅ 5፡ የቆይታ ጊዜና የውሉ መገምገሚያ ጊዜ

1. ይህ ውል ከ....................................... ጀምሮ እስከ ....................................... ድረስ ተፈፃሚ ይሆናል።
2. የውል ማደስ በተመለከተ የውሉ ጊዜ ከማብቃቱ ቢያንስ አንድ ወር በፊት ተዋዋይ ወገኖች አፈፃፀሙን ገምግመው፣ በጽሑፍ በመስማማት ሊያድሱት ይችላሉ።
3. የግንኙነትና ግምገማ ጊዜ፡ ተዋዋይ ወገኖች የአጋርነቱን ዕቅድ አፈፃፀም በየ............................ (ለምሳሌ፡ ሩብ ዓመት) ተገናኝተው ይገመግማሉ።

## አንቀፅ 5፡ የውል ማቋረጥ

ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ውሉ ሊቋረጥ ይችላል፡-

1. የውሉ ጊዜ ሲያልቅ እና በጽሑፍ ካልታደሰ።
2. አንደኛው ተዋዋይ ወገን ቢያንስ ለ30 ቀናት አስቀድሞ በጽሑፍ ማስታወቂያ ሲሰጥ።
3. አንዱ ወገን የውሉን ግዴታዎች ሳይፈጽም ሲቀር እና በጽሑፍ ተነግሮት በ15 ቀናት ውስጥ ማስተካከያ ሳያደርግ ሲቀር።

## አንቀፅ 6፡ ግጭት አፈታት

በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር፣ በመጀመሪያ በውይይትና በሽምግልና ለመፍታት ጥረት ይደረጋል። ስምምነት ላይ መድረስ ካልተቻለ፣ አለመግባባቱ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት በሚመለከተው ፍርድ ቤት ይታያል።

## አንቀፅ 7፡ የስምምነት ማጠቃለያ

**እኛ ከላይ ስማችን የተጠቀሰው ተዋዋይ ወገኖች የዚህን ውል ይዘት ሙሉ በሙሉ አንብበን፣ ተረድተን እና ተስማምተንበት፣ በፊርማችን አረጋግጠናል።**

| የኮሌጁ ተወካይ | የድርጅቱ ተወካይ |
| --- | --- |
| ሙሉ ስም፡ ......................................... | ሙሉ ስም፡ ......................................... |
| ማዕረግ፡ ............................................ | ማዕረግ፡ ............................................ |
| ፊርማ፡ .............................................. | ፊርማ፡ .............................................. |
| ቀን፡ ................................................ | ቀን፡ ................................................ |